በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር

THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA MINISTRY OF FOREIGN AFFAIRS

ፕሬስ መግለጫ PRESSRELEASE

# ኢትዮጵያ እና ግብፅ በሁለትዮሽ እና በባለብዙ ወገን መድረኮች ለመተባበር ተስማሙ



የኢፌዴሪ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ዶ/ር ወርቅነህ ገበየሁ ከግብፅ አቻቸው ሳሜህ ሽኩሪ ጋር በፅ/ቤታቸው ዛሬ ተወያይተዋል፡፡ሚኒስትሮቹ የሁለቱ አገሮች ግንኙነትን የበለጠ ለማጠናከር ተስማምተዋል።

ዶ/ር ወርቅነህ ገበየሁ ሁለቱ አገራት የጋራ ተጠቃሚነታቸውን በሚያሳድጉ ዘርፎች በንግድና ኢንቨስትመንት እንዲሁም በህዝብ ለህዝብ ትስስር ተባብረው እንደሚሠሩ ገልፀዋል።

ግብፅ እና ኢትዮጵያ የረጅም ጊዜ ታሪካዊ ግንኙነት እንዳላቸው የጠቀሱት ዶ/ር ወርቅነህ በኢኮኖሚ መስክ ያለውን ግንኙነት የበለጠ ጠንካራ ወዳጅነት እንዲኖር መስራት ይገባል ብለዋል።

ከታላቁ ህዳሴ ግድብ ጋር በተያያዘ ኢትዮጵያ ከግብፅ እና ሱዳን ጋር ተባብራ መሰራት ትፈልጋለች ብለዋል።

የግብፅ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሳሜህ ሽኩሪ በበኩላቸው ሁለቱ አገራት የረጅም ጊዜ ያስቆጠረ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት እንዳላቸው ጠቅሰው ይህን የበለጠ ለማጠናከር አገራቸው እንደምትሰራ ገልፀዋል።

የህዳሴ ግድብ ዙሪያ ያለውን ንግግር በሶስቱ አገራት ስምምነት የተቋቋመው የባለሙያዎች የጥናት ኮሚቴ እንደሚፈታ ተስፋ እንዳላቸው የግብፅ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ተናግረዋል።

**የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር**

**ቃል አቀባይ ጽ/ቤት**

**ታህሳስ 17 ቀን 2010 ዓ.ም.**

E-mail spokesperson@mfa.gov.et facebook @mfaEthspokesperson, Twitter @mfaEthspokesperson,
YouTube https://www.youtube.com/channel/UCa_KUDpwCLMWyyQIjfilgZg ☎ 011-5-15 8928/011-5-53 6731 Fax 011-5-51-43-00
✉393 Addis Ababa,Ethiopia